ፍኖተ

# ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት ግንቦት 25ቀን 2005 ዓ.ም.


የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

ሁለተኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 78

## ድርጅታዊ ቁመናችን ህዝቡን ለማነቃነቅና ወደ ትግል ለማስገባት የሚችል እንደሆነ እናምናለን

4

የአንድነት ፓርቲ አዲስ አበባ ዞን ሰብሳቢ አቶ ትዕግስቱ አወሉ



## የወረዳ አመራሩ በብአዴን አባላት ቤቴ ተቃጠለብኝ አሉ

3

## ‹‹እናትና አባቴ የሁለት ልጆቻቸው ሀዘን ሰብሯቸው በቅርቡ በሞት ተለይተውናል››

7

ወጣት እዮብ ከበደ የሰኔ አንድ ተማዕታት ማህበር ሰብሳቢ

## የብሄር ግጭትና የኤርትራ ታጣቂዎች ሁመራን አመሷት

8

## በአዲስ አበባ የነፃነት ጥያቄዎች ሲስተጋቡ ዋሉ

7

## የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች በዝዋይ የሚገኙ የህሊና እስረኞችን ጎበኙ

3

## የሰኔ አንድ ሰማዕታት ደም የሚመለሰው በተጠናከረ ትግል ነው

2

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡

ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ስር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ጋዜጣ ነዉ፡፡

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል መርሁ ነው፡፡ ማንኛውም ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን፡፡ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለው ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲውን ለማግለፅ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነው፡፡

## ርእሰ አንቀጽ

# የሰኔ አንድ ሰማዕታት ደም የሚመለሰው በተጠናከረ ትግል ነው

የኢትዮጵያ ህዝብ እስካሁን ባለው የመንግስታት ታሪኩ የሚሻውን ፍትህ የሚያገኝበት ስርዓት ያለተዘረጋለት መሆኑን ቢያውቅም ቀጥቅጠውና ረግጠው ለመግዛት ለሚፈልጉት ሃይሎች ፍጹም ሰላማዊና ያለምንም ሁከት ሃሳቡን መግለጽ የሚችል ስልጡን መሆኑን ከማሳየት ወደ ኋላ ብሎ አያውቅም፡፡የኢህአዴግ ሊቀ መንበር የነበሩት መለስ ዜናዊ ግንቦት ሰባት ቀን በሚቆጣጠሩት ብሄራዊ ቴሌቪዥን ቀርበው ጣቱን የሚያወጣን እንደሚቆርጡ ቢዝቱም ሰላማዊው ህዝብ መንግስትንና የአገርን ሉአላዊነት ለማስከበር ነፍጥ ያነገቱ ወታደሮችን በማመን በሰላማዊ መንገድ ድምጹን ለማሰማት አደባባይ ወጣ፡፡ ነገር ግን እንዳለመታደል ሆኖ ህዝብን ለመጠበቅ በባንዲራው ስር ተንበርክከው ቃል የገቡ ወታደሮች፣ የፌደራል ፖሊሶችና በገዢው ቡድን የተደራጁት አልሞ ተኳሶች ድምጻቸውን ከሌቦች ለማስጣል ጩህት ያሰሙ ዜጎችን፣ ከትምህርት ቤት የሚመለሱ ህጻናትን፣በየመንገዱ ያገኟቻን ሴቶችና አዛውንቶችን በጥይት አረር ቀጠቀጡ፡፡

አዲስ አበባች በደም ጨቀየች፡፡ኢህአዴግ አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ ደርግ በግፍ ገድሎ በጅምላ መቃብር የቀበራቸውን አስከሬኖች እያስወጣ የለቅሶ ወግ ያልደረሳቸውን ቤተሰቦች አስከሬኖቻቸውን በወጉ እንዲቀብሩ ያደረጉ ሃይሎች በተራቸው ሰላማዊ ንጹሃን ዜጎችን ያለ ርህራሄ ቀጠፉ፡፡ “ሰው በላው ስርዓት በመውደቁ ከአሁን በኋላ ልጆቻችሁን በነጻነት ታሳድጋላችሁ” የተባሉ እናቶች ኢህአዴግም ሰው በላ መሆኑን የሰኔ አንድ 1997 የፈፀመው ኢሰብአዊ ድርጊት ማስረጃ ይሆናቸዋል፡፡

ደርግ በዘመኑ የኢህአፓ ወጣቶችን በአደባባይ በመረሸን ለህዝቡ ያስተላለፈው መልእክት አንድና አንድ ነበር ይህ መልእክት የገባው ህዝብም ወደ ፍርሃት ጠርሙሱ በመግባት አምባገነኑን ስርዓት ለ17 ዓመታት በጫንቃው ተሸከመ፣ለለውጥ ያጎፈሩት ኢህአዴጎች በበኩላቸው ህዝቡን ነጻ ለማውጣት መታገላቸውን አብስረውት የነበረ ቢሆንም ከስልጣናቸው በላይ ምንም ነገር እንደሌለ በወሰዱት ኢ- ፍትሃዊ እርምጃ አሳይተዋል፡፡

መጪው ሳምንት በ97 ምርጫ ህይወታቸውን ያጡ ወገኖቻችንን የምናስብበት ስምንተኛ ዓመት ነው ፡፡ በዚህ ቀን አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሰማዕታቱን ከማሰብ ጎን ለጎን መንግስትን፣ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መዘርጋት የሚታገሉ ኃይሎችን፣ ማህበረሰቡንና በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ተቋማትን ቆም ብለው ያለፉበትን መንገድ እንዲፈትሹ ይጠይቃል፡፡

ማህበረሱቡ የሰጠውን ድምጽ በትክክል ቆጥሮ የሚያስረክብ ተቋም በማጣቱ ምርጫን በአገራችን የካርኒቫል ያህል የምናከብርበትና በጉጉት የምንጠብቅበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡ በ2002 እና በ2005 በተደረጉ አገር አቀፍና ክልላዊ ምርጫዎች የታየው መፋዘዝና ተሳታፊ ማጣት በምርጫ 97 የተፈጠረው ምስቅልቅል ውጤት ነው፡፡ የቀበሌና የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች የምርጫን ምህዳር ለመፍጠር ህዝቡን ጠዋትና ማታ እያስጨነቁ ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች እንዲያመራ ማድረጋቸው መንግስት ራሱን ለመሸንገያነት እስካልተጠቀመበት ድረስ ህዝቡ በተቋማቱ ላይ ያለው እምነት ተሸርሽሮ አስፈሪ የሚሰኝ ደረጃ ላይ መድረሱን የህዝቡን ትርታ በማዳመጥ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምርጫው በጥቁር መዝገብ ላይ እንዲሰፍር ማቀጣጠያ ከሆኑት ነገሮች መካከል ምርጫ ቦርድና ፍርድ ቤቶች በነጻነታቸው ዙሪያ ጥያቄ ውስጥ የሚከቷቸውን ነገሮች መፍጠራቸው ነው፡፡ መንግስት ለነጻ ምርጫ መከናወን በየማለዳው ከሚነግረን ዲስኩር በተጨማሪ በእነዚህ ተቋማት ዙሪያ የሚነሱበትን ውሃ የሚቋጥሩ ጥያቄዎች በተገቢው መንገድ መመለስ ይኖርበታል፡፡

ማህበረሰቡ አጠገቡ የነበሩ ልጆቹ በአምባገነኖች ጥይት ሲቆሉ እየተመለከተ ወደ ፍርሃት ጠርሙስ መግባት ሳይሆን ልጆቹ ያነሱት ጥያቄ ተገቢ መሆኑን በማመን አምባገነን ስርዓትን የምሸከምበት ጫንቃ የለኝም ማለት ይጠበቅበታል፡፡ ያን ግዜም ህይወታቸውን ያጡ የምርጫ ሰማዕታት ትክክለኛውን መታሰቢያ ያገኛሉ ፡፡ ይህ ሲሆም የሰማዕታቱ ደም በከንቱ ፈሶ አለመቅረቱን ታሪክ ህያው ምስክርነቱን ይሠጣል፡፡

ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚታገሉ የሠላማዊ ታጋዮች መስዋዕትነት ትግላቸው ፍሬ ሊያፈራ የሚያስችለው ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በመገንዘብ በሰላማዊ ትግላቸው ሊገፉበት ይገባል እንጂ አንድ ጋት ወደ ኋላ መመለስ እንደሌለባቸው አንድነት ያምናል፡፡ እርግጥ ነው የቤተሰባችንን አባላት በህይወት ማጣት ህመም ይፈጥራል ነገር ግን ዜጎቻችን መስዋዕትነት የከፈሉበት አላማ ግቡን እንዲመታ እጅ ለእጅ በመያያዝ በሰላማዊ ትግል ወደ ፊት ልንል ይገባናል፡፡ በወርሃ ሰኔ የመጀመሪያ ቀን ያጣናቸው ወገኖቻችን ደም እንደ አቤል የሚጣራውም ፍጹም ሰላማዊ፣ዜጎቿ የሚኮሩባት፣ለቡድን ሳይሆን በትክክል ከህዝብ ጎን የሚቆሙ ህዝባዊ ወገንተኝነት ያላቸው ተቋማት ያሉዋትን አዲሲቷ ኢትዮጵያን ነው፡፡

ጋዜጣችንን “ፍኖተ ነፃነት“ ብለናታል “ፍኖት“ ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር የነፃነት መንገድ ማለት ነው፡፡

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች በዝዋይ የሚገኙ የህሊና እስረኞችን ጎበኙ



የአንድነት ፓርቲ የእስረኞችና የእስረኛ ቤተሰቦች ድጋፍ ሰጪ ቡድን ያዘጋጀውና የፓርቲው ሊቀመንበር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና የብሄራዊ መ/ቤት ሰብሳቢ አቶ ዘካርያስ የማነብርሀን ጨምሮ ስራአስፈጻሚዎች፣የብሄራዊ ም/ቤት አባላትና የእስረኛ ብተሰቦች የተካተቱበት ቡድን በዝዋይ እስር ቤት የሚገኙ የህሊና እስረኞችን ግንቦት 24 ቀን 2005 ዓ.ም ጠይቀዋል፡፡

ጉንኝቱ የተዘጋጀው የህሊና እስረኞችንና ቤተሰቦቻቸውን ለመደገፍ በተቋቋመው ኮሚቴ ሲሆን በጉብኝቱ የአንድነት ፖርቲ ብሔራዊ ምክር ቤሰብሳቢና አባላት እና የህሊና እስረኛ ቤተሰቦች ተካፍለዋል፡፡

ዶ/ር ነጋሶ ጉብኝታቸውን አስመልክተው ለፍኖተ ነፃነት የሚከተለውን ተናግረዋል‹‹የአንዷለምና የናትናኤል ቤተሰቦች ከእኛ ጋር አብረውን የተጓዙ ሲሆን የጋዜጠኛ ውብሸት ባለቤት በዕለቱ ፈተና ስለ ነበረባት አብራን ለመጓዝ አልቻለችም፡፡ እስረኞቹ በዝዋይ የሚገኙ ቢሆንም እነርሱን በአንድነት መጠየቅ የማይቻል በመሆኑ በሁለት ቡድን ተከፍለን መጠየቅ ነበረብን፡፡ በማረሚያ ቤቱ አርባ ክፍሎች መሆናቸውን ተረድተናል፡፡ከእነዚህ ክፍሎች ሁለቱ የተለዩ ናቸው፡፡በዚህ ውስጥ የሚገኙት እነ ዘሪሁን ናቸው፡፡በማረሚያ ቤቱ አንድ መጸዳጃ፣አንድ ገላ መታጠቢያ የሚገኝ ሲሆን አንድ አነስተኛ ክሊኒክ እንደሚገኝ ለማወቅ ችለናል፡፡ የታሳሪዎቹ ሁኔታ ሊለወጥ የሚችለው ሰላማዊ ትግሉ ሲበረታታና ሰዎች እነዚህን ሰዎች በመጠየቅ ድጋፉን ሲገልጽላቸው ነው፡ ፡እዚህ ላይ ማንሳት የሚኖርብኝ አቶ በቀለ ገርባ ስሜቱ በጣም ተነክቶ በደስታ ሲያነባ ነበር፡፡ሰላማዊ ታጋዮች ሲታሰሩ ቤተሰቦቻቸው በእነርሱ ምክንያት ጉዳት ላይ እንዳይወድቁ ማገዝ የሰላማዊ ታጋዮች መለያ መሆን እንደሚገባው በዚህ አጋጣሚ መልእክቴን ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡››

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የህዝብ ግኑኝነት ሃላፊ የሆነው ወጣቱ ፖለቲከኛ አቶ ዳንኤል ተፈራ በዝዋይ ማረፊያ ቤት የሚገኙትን የህሊና እና የፖለቲካ እስረኞችን ለመጠየቅ በስፍራው ከተገኙ የፓርቲው አመራሮች አንዱ ነው፡፡ዳንኤል ከጉብኝቱ መልስ ለፍኖተ ነጻነት በሰጠው አስተያየት‹‹የአንድነት አመራሮች በማረሚያ ቤት የሚገኙ ፖለቲከኞችንና የህሊና እስረኞችን ለመጠየቅ ሲያመሩ የመጀመሪያ ጊዜያቸው አይደለም፡፡በቂሊንጦና በቃሊቲ ማረሚያ ቤቶች የሚገኙትን እስረኞች ለመጠየቅ በተንቀሳቀሱባቸው አጋጣሚዎች ግን ወደ ውስጥ በመዝለቅ የሚፈልጓቸውን ሰዎች እንዳይገናኙ መደረጋቸው አይዘነጋም፡፡በዝዋይ የሚገኙትን ታሳሪዎች ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬን ጨምሮ ፖለቲከኞቹን ናትናኤል መኮንን፣አንዷለም አያሌው፣ ሻምበል የሺዋስ ይሁን፣በቀለ ገርባ፣ ሌሊሳ ኦልባና ፣ ዘሪሁን ገ/እግዚአብሄርንና ሌሎችን ጠይቀናል፡፡ የዝዋይ ማረሚያ ቤት ከሌሎቹ ማረሚያ ቤቶች በተለየ ሰዎቹን እንድንጠይቅ መፍቀዱ ሊበረታታ ይገባል፡፡ከሰላማዊ ታጋዮቹ ጋር በነበረን የ30 ደቂቃ ቆይታ በማረሚያ ቤቱ ስለ ተያዙበት ሁኔታ በአጠቃላይ ስላለው ነገር አነጋግረናቸው ተመልሰናል፡፡የአንድነት ፓርቲ በዚሁ አጋጣሚ ከእስረኞቹ ጎን በመቆም እስከ መጨረሻው ድረስ ወደ እስር ቤት የገቡበትን አላማ በማንገብ እንደሚታገል ቃል ገብቶላቸዋል፡፡››

# የወረዳ አመራሩ በብአዴን አባላት ቤቴ ተቃጠለብኝ አሉ

በቤንሻንጉል ክልል የአሶሳ ወረዳ የአንድነት ፓርቲ ሰብሳቢ የአቶ አለባቸው አሰፋ ቤት በብአዴን አባላት እንዲቃጠል መደረጉን ለፍኖተ ነፃነት አስታወቁ፡፡

የአቶ አለባቸው አሰፋ ቤትየተቃጠለው ግንቦት 12,2005 ዓ.ም ከምሽቱ 3 ሰአት ከ30 ገደማ እንደሆነ ታውቋል ግለሰቡ ስለቤታቸው መቃጠልና ስለወደመባቸው ንብረት ለፍኖተ ነፃነት ሲስረዱ “ሰኞ ግንቦት 12 ቀን ከምሽቱ 3፡30 ቤቴ በእሳት ቃጠሎ ከ30000- 40000 ብር የሚገመት ቤትና 15 እግር ማንጎ ሙሉ በሙሉ ወደመ እኔ ቤት አልነበርኩም፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች እሳቱን ለማጥፋትና እኔ ቤት ውስጥ ያለሁ መስሎአቸው ለማዳን ቢታገሉም ቤቱ ሙሉ በሙሉ ወደመ እኔ በቤት ውስጥ ባለመኖሬ ተርፊያለሁ፡፡” ብለዋል፡፡

ከምርጫ 97 ጀምሮ በፖለቲካ ትግል ውስጥ እንደተሳተፉ የሚናገሩት አቶ አለባቸው በዚሁ የፖለቲካ ተሳትፏቸው ሰበብ ለእስርና ለእንግልት መዳረጋቸውን ያስረዳሉ፡ ፡ በቤታቸው ላይ ስለደረሰው የተቀነባበረ የዝሳት አደጋ አስመልክተው ለሚመለከተው መንግስት አካልአስረድተው እንሆነ የተጠየቁት አቶ አለባቸው “ለወረዳ ፖሊስም አመለከትኩ የጠረጠርኳቸውንም ሰዎች የጠረጠርኩበትን ምክንያትና ማስረጃዎችም እንዳሉኝ የአካባቢው ነዋሪም እንደሚመሰክርልኝ አስረዳሁ፡፡ ምንም ማድረግ አንችልም ያቃጠሉትን ያየ ሰው ካለ አምጣ ብለው አቤቱታዬን ሊቀበሉ አልቻሉም፡፡ መርዝ ሊያጠጡኝ እንደነበረ በኤግዚቢትነት የተያዘ ማስረጃ አለ፡፡ እነዚህን እንደመነሻ ይዛችሁ ምርመራ አድርጉልኝ ቦታው ድረስ ሄዳችሁ የተቃጠለውን እዩልኝ ሜዳ ላይ ነው ያለሁት፡፡” በማለት አቤቱታ ማቅረባቸውን ተናግረዋል፡፡ አክለውም ይህን የግድያ ሙከራ እየፈጸሙ ያሉት የብአዴን አባላት መሆናቸውን ፖሊስ ጭምር እንደሚያው አስረድተው “ይህን ድርጊት የሚፈፅሙት በአካባቢው ያሉ የብአዴን አባላት ናቸው ሲዝቱብኝም ፖሊስ ሰምቷል፡፡

የሚሰማኝ አካል አጣሁ ግራ ገብቶኛል፡፡” በማለት በአካባው ያለውን የፍትህ ችግር አጋልጠዋል፡፡

ስለተከሰተው የንብረት ውድመትና የግድያ ሙከራ የፖሊስን ምላሽ ለማካተት ወደ አሶሳ ወረዳ መስተዳድርና ፖሊስ በተደጋጋሚ ብንደውልም ምላሽ ባለማግኘታችን ለማጣራት ያደረግነው ጥረት አልተሳካም፡፡

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# “ድርጅታዊ ቁመናችን ህዝቡን ለማነቃነቅና ወደ ትግል ለማስገባት የሚችል እንደሆነ እናምናለን”

## የአንድነት ፓርቲ አዲስ አበባ ዞን ሰብሳቢ አቶ ትዕግስቱ አወሉ

**የዚህ ሳምንት እንግዳችን የአንድነት ፓርቲ ብሄራዊ ምክር ቤት ጸሀፊና በቅርቡ ዳግም ተጠናክሮ በተዋቀረው የአዲስ አበባ ዞን ሰብሳቢ አቶ ትዕግስቱ አወሉ ናቸው፡፡ አንድነት ፓርቲ በአዲስ አበባ ዞን ለመስራት ስላቀዳቸው ተግባራትና በአዲሱ የዞን ምክር ቤት አወቃቀር ዙሪያ ከፍኖተ ነፃነት ጋር ያደረጉትን ቆይታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡**



**ፍኖተ ነፃነት፡- በቅርቡ የአንድነት ፓርቲ የአዲስ አበባ ዞንን ለማጠናከር አዳዲስ የምክር ቤትና የስራ አስፈፃሚ አባላትን መርጧል፡፡ ከአዲሱ እራ አስፈፃሚ ምን እንጠብቅ?**

አቶ ትዕግስቱ፡-የአሁኑ የምክር ቤት አመሰራረት መነሻ የሆነው የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ብሔራዊ ስራ አስፈፃሚና የፓርቲው ድርጅት ጉዳይ ኮሚቴ በጋራ በቀድሞው የአዲስ አበባ ዞንን ከገመገሙ በኂላ የዞኑ ምክር ቤትም ዞኑ ዳግም እንዲዋቀር መወሰኑ ነው፡፡ የቀድሞው የዞን ምክር ቤት የነበረውን ጠንካራ ጎን በመያዝ ድክመቱን በማስወገድ አዲሱ ምክር ቤት፣ የአንድነት ፓርቲን አላማና እቅድ በመተግበር ፓርቲው ከአባላቱ፣ ደጋፊዎቹና ከህዝቡ እንዲያከናውን የሚጠበቅበትን ሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴ ለማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡ በተለይም በዋቅሩን እታች ድረስ በመዘርጋት የፓርቲውን አላማ ሊያስፈፅም የሚያስችል፣ ሰላማዊውን ትግል ከግብ ለማድረስ ለሚደረገው የህዝብ ንቅናቄ መሰረት ሊሆን የሚችል ድርጅታዊ መዋቅር ለመፍጠር አቅዶ እየሰራነው፡፡ ምክር ቤቱ አባላት በትምህርት ዝግጅታቸውና በትግል ተሞክሯቸው ለሰላማዊ ትግሉ መፋጠን አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ናቸው፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- በግምገማ በቀድሞው አዲስ አበባ ምክር ቤት ላይ የታዩትን ድክመቶች ለማረምና ጥንካሬዎቹን ይዞ ለመቀጠል ምን በማድረግ ላይ ናችሁ?**

አቶ ትዕግስቱ፡- እንግዲህ እኔ የምመራው ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተመረጠው ግንቦት 11, 2005 ዓ.ም ነው፡፡ ስራችንን የምንሰራው በምዕራፍ በመከፋፈል ነው፡፡ የቀድሞው የዞን ምክር ቤት የግምገማ ውጤት መርምረን ጥንካሬዎቹን የበለጠ በማጠናከር ድክመቶቹን እንቀርፋለን፡፡ የቀድሞው ምክር ቤት ሰፋ ያለና ጥልቀት ያለው እቅድ አዘጋጅቶ ነበር ከዛ ውስጥ የተፈፀሙትን እና ያልተፈፀሙትን በመለየት ያልተፈፀሙት ለምን እንዳልተፈፀሙ እንፈትሻለን፡፡ የዞናችን 23 ወረዳዎች በግብረሀይል ደረጃ ተገምግመው ነበር በመሆኑም የዛንም ግምገማ ውጤት መርምረን ወረዳዎቻችንን አንድነትን በሚመጥን ደረጃ ለማጠናከር እንሰራለን፡፡ ይሄን የ3 ወር የሽግግር ጊዜ እቅዳችንን ሰኔ 9 በሚጠራው የመጀመሪያው የምክርቤት ስብሰባ እናስፀድቃለን፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- አዲሱ የዞን ምክር ቤት ጥንካሬ ከስብጥር አንፃር ምን ይመስላል?**

አቶ ትዕግስቱ፡- በፓርቲያችን ደንብ መሰረት የአዲስ አበባ ዞን ምክር ቤት ከሁሉም የዞኑ ወረዳዎች ተመርጠው በሚወከሉ ሁለት፣ሁለት ሰዎች ነው፡፡ በመሆኑም ምክር ቤታችን 46 አባላት አሉት፡፡ ከነዚህ የምክር ቤት አባላት በካከል ከ72 በመቶ በላይ የሚሆኑት ወጣቶች ናቸው፡፡ በትምህርት ዝግጅት በኩል ምክር ቤቱን ስንመለከተው የመጀመሪያ ዲግሪና ከዛ በላይ ያላቸው የምክር ቤቱ አባላት ከ45 በመቶ በላይ ሲሆኑ የተቀሩት ዲፕሎማ ያላቸው ናቸው፡፡ ከዛ በታች የሆኑት ከ5 በመቶ አይበልጡም፡፡ የሴቶች ተሳትፎ አነስተኛ በመሆኑ በዚህ ረገድ ብዙ መሰራት ያለበት ይመስለኛል፡፡ የስራ አስፈፃሚውን ሁኔታም ስንመለከት ካሉት 9 የዞን አመራሮች ሁለቱ ማስትሬት ዲግሪ ሲኖራቸው አራቱ የመጀመሪያ ዲግሪ አላቸው፤ የተቀሩት ዲፕሎማ አላቸው፡፡ በእድሜም በኩል አመራሮቹ ከ27 እስከ 45 አመት ሲሆኑ ሰባቱ ከሰላሳ አመት በታች ናቸው፡፡ ከዛ በተጨማሪም ከስራ አስፈፃሚዎቹ መካካል አንዷ ሴት ናት፡፡ የዞኑ ምክር ቤትና ስራ አስፈፃሚው ካለው የትምህርት ዝግጅትና የትግል ልምድ አንፃር በፓርቲው ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡ ከዚህ ቀደም ከነበረው በተሻለ ደረጃ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀማችንን ለማዘመንም በስራ አስፈፃሚ ደረጃ የመረጃ ክትትልና ኩነቶችን የሚያከታተል አመራር አካተናል፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- ለሰላማዊ ትግል መሰረት የሚሆነው ህዝቡን ለለውጥ ማንቀሳቀስ ነው፣ የዞኑ ምክር ቤትና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ለዚህ ምን ያክል ብቁ ነው?**

አቶ ትዕግስቱ፡- ህዝባዊው ንቅናቄ መሰረት የሚያደርገው በቅድሚያ የፓርቲው አባላት ላይ ነው፤ በመቀጠልም ደጋፊዎቹን ማስተባበር ነው፡፡ ከዛም ይህ እንቅስቃሴ ወደ ህዝቡ በተለያየ መንገድ ሲደርስ የለውጥ እንቅስቃሴዎች ይጀመራሉ፡፡ ለሰላማዊ ትግል ስኬታማነት በእውቀት ላይ የተመሰረተና የታቀደ ስራ ማከናወን አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን፡፡ በአሁኑ የሽግግር ጊዜ እቅድ ላይ ወረዳዎችን የበለጠ የማጠናከር እንሰራለን፡፡ ለወረዳ አመራሮችና አባላት የተለያዩ የአጭር ጊዜ ስልጠናዎችን በመስጠት ለለውጥ የሚያበቃ የትግል ቁመና እንዲኖራቸው እንሰራለን፡፡ አለም አቀፍ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሰላማዊ ትግል ከ200 በላይ የሆኑ ስልቶች አሉት ከእነዚህን ስልቶች መካከል ለኢትዮጵያ ሁኔታ ምቹ የሆኑትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ዝግጅት አለን፡፡

ይህ ድርጅታዊ ቁመና ህዝቡን ለማነቃነቅና ወደ ትግል ለማስገባት የሚችል እንደሆነ እናምናለን፡፡ በተለይም በአዲስ አበባ ደረጃ በተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥና በተለያዩ የሲቪክ ተቋማት ውስጥ ያሉ ወጣቶችን የለውጥ ኃይል እንዲሆኑ የሚያስችል ስራ በመስራት ወደ ፓርቲው ለመሳብ አንድነት የጀመረውን ስኬታማ ጥረት አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡ በርግጥ ሁሉም አባል እንዲሆኑ አንጠብቅም በጋራ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በመወያየት የትግሉ አካል እንዲሆኑ ማድረግ ነው፣ ስለዚህ ከፓርቲው ውጪ ሆነው ለለውጥ መታገልና አሁን ኢትዮጵያ ያለችበትን አስከፊ ሁኔታ መቀየር ያስፈልጋል፡፡ በአጠቃላይ ህዝቡን ለማስተባበር የሚያስችል አቅም አለን፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- ዘመኑ የቴክኖሎጂ እንደመሆኑ ሰላማዊ ትግልንም በኮሚውኒክሽ ቴክኖሎጂ መንገድ መቃኘት ያስፈልጋል በዚህ ረገድ ምን አስባችኂል?**

አቶ ትዕግስቱ፡- አንድነት እንደሚያምነው

ወደገፅ5 ዞሯል

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# የአንድነት አባላትን ማሰርና ማወከቡ ቀጥሏል

የአንድነት ለዴሞክራሲና ፍትህ ፓርቲ አባላት በሆኑ ዜጎች ላይ የእስር ዘመቻ መከፈቱን የፓርቲው አመራሮች ለፍኖተ ነጻነት በሰጡት መረጃ አጋለጡ።የፓርቲው አባላት እስራት የተፈጸመባቸው በአዲስ አበባ፣ጎንደር፣ወላይታ፣ቤንሻንጉልና በአፋር ክልልሎች ነው።

አቶ ተገኝ ሲሳይ በጎንደር የምዕራብ አርማጭሆ የአንድነት ሰብሳቢ ። ለስራ ባመሩበት ሁመራ ውስጥ ከለሊቱ ስድስት ሰዓት በቁጥጥር ስር በማዋል የአካባቢው ታጣቂዎች ከፍርድ ቤት ትእዛዝ ውጪ አቶ ተገኝ ያረፈበትን ሆቴል በመበርበር በኪሳቸው ውስጥ የአንድነት ፓርቲና የሰመጉ አባል መሆናቸውን የሚያስረዳ መታወቂያ ሲያገኙ ድብደባ በማድረስ ለሁለት ቀናት የተለያየ ኢሰብዓዊ ድርጊት ሲፈፀምባቸው ከቆዩ በኋላ ከሌሎች ዘጠኝ እስረኞች ጋር በአንድ ፒካፕ መኪና በመጫን ወደ ጎንደር እንዲመለስ አድርገውታል።

የአቶ ተገኝ ቤተሰቦች እስረኛውን ለመጠየቅ ከፖሊስ ፈቃድ ባያገኙም ከሌሎች እስረኞች በደረሳቸው መረጃ ተገኝ የትኛው የጎንደር ፖሊስ ጣብያ እንደሚገኝ ለማወቅ ችለዋል። በጎንደር የአንድነት አባላት ፖሊስን ለማናገር ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም ፖሊስ በአደራ የተረከብኩት እስረኛ በመሆኑ እኔ ፍርድ ቤት ላቀርበው አልችልም እንዳላቸው ገልጸዋል።

በደቡብ ወላይታ ዞን ዳሞት ወይዴ ወረዳ የአንድነት አባሉ አቶ ያኒቶ ወጋሶ በ2003 ዓ.ም በዞኑ የገቢዎች መስሪያ ቤት ሰርተዋል፡ ፡ታጋዩን በምክንያት ለማሰር ሲያሴሩ የነበሩ የዞኑ አስተዳዳሪዎች አቶ ያኒቶ ገቢዎችን ከለቀቁ ከአመት በኋላ በፖሊስ ቁጥጥር ስር እንዲውሉ አድርገዋል።ፖሊስ ያኒቶን ያሰረበትን ምክንያት እንዲያብራራ ተጠይቆ ‹‹ያኒቶ ገቢዎች ይሰሩ በነበረበት ወቅት ከ2002-2004 ለነጋዴዎች ከግብር ነጻ የሚያደርጋቸውን ወረቀት ይሰጡ እንደነበር መረጃ ደርሶኝ ነው›› ማለቱን በዞኑ የሚገኙ የአንድነት አባላት ይናገራሉ።ያኒቶ የተሳሳተ

ደረሰኝ ሰጡ በተባለበት አመት ግን በስፖርት ጽ/ቤት ይሰሩ ነበር። አቶ ያኒቶ ለአምስት ቀናት ያህል ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ በመታወቂያ ዋስ እንዲለቀቁ መደረጋቸው ተሰምቷል። በአዲስ አበባ ኢህአዴግ አዲስ አበባን የተቆጣጠረበትን 22ኛ ዓመት በሚያከብርበት ግንቦት 20ቀን 2005 ዓ.ም የአንድነት ፓርቲ የአዲስ አበባ ዞን የወረዳ 19 ምክትል ሰብሳቢ የሆነው አቶ ባህሩ ራህመቶ ከመኖሪያ ቤቱ የደንብ ልብስ ባልለበሱ ሁለት የደህንነት አባላት ተወስዶ ለቀናት ያለበት ፖሊስ ጣብያ ሳይታወቅ ቆይቷል። ቤተሰቦቹና የወረዳው የአንድነት አመራሮች ባደረጉት ፍለጋ ባህሩ በማዕከላዊ ምርመራ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። በግንቦት ሰባት አባልነት ተጠርጥሮ ስለ መታሰሩ ይፋዊ ባልሆነ መንገድ ከተገኘ መረጃ ውጪ ፖሊስ የአንድነቱን የወረዳ አመራር ለምን እንዳሰረው ለማንም ከመግለጽ መቆጠቡንና በቤተሰቦቹም ሆነ በሌሎች እንዳይጎበኝ መከልከሉ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌን የሚጻረር ነው።

የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር የሆነው አቶ አንዷለም አራጌን ጨምሮ የብሄራዊ ምክር ቤት አባል የሆነው አቶ ናትናኤል መኮንን በእስር ላይ የሚገኙ መሆናቸውም ይታወቃል።

# ሁመራን የብሄር ግጭትና የኤርትራ ታጣቂዎች አመሷት

በምዕራብ ሁመራ ማይካራ መቻች በተከሰተ የብሔር ግጭት የሰዎች ህይወት ጠፋ፤ መንግስት ግጭቱን ለማስቆም የወሰደው እርምጃ አለመኖሩ በአካባቢው ተከታታይ ግጭቶች ሊቀሰቀስ ይችላል የሚል ስጋት መፍጠሩን የአካባቢው ምንጮች ለፍኖተ ነፃነት አስታወቁ።

ሱዳን ጠረፍ ላይ ቅዳሜ ግንቦት24 ቀን 2005 ዓ.ም በብሄር ምክንያት የተቀሰቀሰው ይኸው ግጭት በሁለት ቀናት ውስጥ የ12 ሰዎችን ህይወት መቅጠፉንፉን የፍኖተ ነጻነት ምንጮች ጨምረው ገለፀዋል። በኢትዮጵያና ሱዳን ጠረፍ አካባቢ በምትገኘው መቻች በረሃ በቀን ስራ የተሰማሩ ሰዎች በብሄር እየተቧደኑ መገዳደል ከጀመሩ ሶስት አመታት ማስቆጠራቸውን ያስታወሱት ምንጮቻችን መንግስት ችግሩን ለመፍታት ምንም አይነት ሚና ለመጫወት አለመፍቀዱ የሚቾቹንና የተጎጂዎቹን ቁጥር እንዲያሻቅብ አድርጓል። ሰራተኞቹ በወሎ፣በጎጃም፣በጎንደርና በራያ ተወላጅነት ተቧድነው በካራ፣በዱላና በእሳት በፈጠሩት ግጭት የሰው ህይወት ተቀጥፏል።

በጉዳዩ ዙሪያ ያነጋገርናቸው አካባቢውን ጠሚያውቁ አስተያየት ሰጪዎች "መንግስት በኢትዮጵያ የብሄር ጥያቄ ተመልሷል በማለት የብሄር ብሄረሰቦችን በዓል በሚያከብርበት ወቅት በጎሳ ፖለቲካ እንዲህ አይነት ዘግኛኝ ድርጊቶች እየተፈጠሩ የሰው ህይወት መብላታቸው ጥያቄዎቹ በተገቢው መንገድ ላለመመለሳቸው ማሳያ ይሆናል" ብለዋል።

በተያያዘ ዜና በዚሁ በሁመራ በረከት ወረዳ ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ለመዝረፍ የሚሞክሩ ሽምቅ ተዋጊዎች በተለያዩ ጊዜያት ድንገተኛ ወረራ በማድረግ የአካባቢውን ነዋሪዎች ሲያስጨንቁ እንደነበር የጠቀሱት ምንጮቻችን በቅርቡ ታጣቂዎቹ አካባቢውን ከሚጠብቁ ሚልሺያዎች ጋር ባደረጉት የተኩስ ልውውጥ በሁለቱም ወገን ህይወት መጥፋቱን አጋልጠዋል። በተደጋሚ የማያባራ የተኩስ ልውውጥ መስማት በአካባቢው የተለመደ እንደሆነም የፍኖተ ነፃነት ምንጮች ጨምረው ገልፀዋል።

በሁመራ ስለተከሰተው የግጭት ለማጣራት የአካባቢውን ባለስልጣናትና የፖሊስ ለማግኘት ያደረግነው ጥረት አልተሳካም።

## ድርጅታዊ ቁመናችን ህዝቡን...

ትግሉን ስኬታማ ለማድረግ በእውቀት ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት እናምናለን። በመሆኑም የተለያዩ ስልጠናዎች ለአመራሮችና ለአባላት በመሰጠት ላይ ናቸው። የአዲስ አበባ ዞን በቅርቡ ፓርቲው ያሉትን በርካታ ምሁራን ተጠቅሞ ስልጠናዎችን ለመስጠት አቅዷል፡ ፡ በተለይም የኢንተርኔ ቴክኖሎጂን በአግባቡ ተጠቅሞ ትግሉን ለማጠናከር እንቅስቃሴ ጀምረናል። በተጨማሪም ፓርቲያችንን በማህበራዊ ሚዲያ የማስተዋወቅ፣ ለህብረተሰቡ መረጃ የማቀበልና የማስተባበር ተግባራረትን አባላቶቻችን እንዲሰሩ ለማድረግ ስልጠናዎችን በተከታታይ እንሰጣለን።

**ፍኖተ ነፃነት፡- በቅርቡ ሰኔ አንድ ለማድረግ ያቀዳችሁት ፕሮግራም እንዳለ ይታወቃል፤ ዝግጅቱ ምን ይመስላል?**

አቶ ትዕግስቱ፡- እንደሚታወቀው ፓርቲያችን በሰላማዊ ትግል መድረኩ ከፍተኛ ዋጋ በመክፈል ላይ ያለ ፓርቲ ነው። የህሊና

## ከገፅ5 የዞረ

እስረኞችን ለማሰብ ወር በገና በሶስተኛው ቀን የሻማ የማብራትና የተለያዩ ዝግጅቶች ይደረጋሉ።ይህን ዝግጅት በመጪው ሰኔ አንድ በ1997 በግፍ የተገደሉ ሰማዕታትንም ለማሰብ ልናውለው ተዘጋጅተናል። የ97 ሰማዕታትን ለማሰብና የህሊና እስረኞችን በጋራ ለማሰብ ለሚደረገው ዝግጅት ኀሚቴዎችን በማዋቀር ዝግጅቶችን በማድረግ ላይ ነን። የሰኔ አንድ ሰማዕታት ማህበርም አብሮን በመስራት ላይ ይገኛል።

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# በአዲስ አበባ የነፃነት ጥያቄዎች ሲስተጋቡ ዋሉ

ሰማያዊ ፓርቲ በጠራውና በአስር ሺ የሚቆጠሩ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የተሳተፉበት ሰላማዊ ሰልፍ በተሳካ ሁኔታ በሰላም ተጠናቀቀ፡፡

መነሻውን አራት ኪሎ /በተለምዶ ግንፍሌ/ አካባቢ ከሚገኘው የሰማያዊ ፓርቲ ጽ/ቤት ያደረገው የተቃውሞ ሰልፍ በአራትኪሎ፣ በፒያሳ፣በቸርችል ጎዳና አድርጎ ኢትዮ ኩባ ወዳጅነት አደባባይ ደርሷል፡፡ ዜጎች በፍርሃት የሚኖሩበት ዘመን ብቃ፣ የታሰሩት ይፈቱ፣ አሸባሪ አይደለንም፣ሁሉም የመንግስት ሌቦች ለፍርድ ይቅረቡ፣ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ጥያቄዎች ይመለሱ፣ ቋንቋን መሰረት ያደረገ ማፈናቀል ይቁም፣ አንድነን አንለያይም፣ ፍትህ እያሉ ቃሊቲ ገቡ፣መማር ያሳስራል ቃሊቲ ያስገባል ሰልፈኞቹ ካሰሟቸው መፈክሮች መሀከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ሙስሊሙ የህብረተሰብ በሰልፉ ላይ በከፍተኛ ቁጥር ተገኝቶ ድምፁን በከፍተኛ ደረረጃ አሰምቷል፡፡

በኢትዮኩባ አደባባይ ለተሰበሰበው ሰልፈኛ የእለቱ የክብር እንግዶች ዶክተር ያዕቆብ ኃይለማርያም፣የጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ አባት አቶ አለሙ ጎቤቦ እንዲሁም በቅርቡ የተፈናቀሉት አማሪኛ ተናጋሪ ዜጎች ተወካይ አቶ ሃብታሙ ስንሻውና የሙስሊሙ ህብረተሰብ ተወካዮች ንግግር አድርገዋል፡፡ በመጨረሻም ንግግር ያደረጉት የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር ኢ/ር ይልቃል ጌትነት ሰልፉን ያዘጋጁትን የፓርቲያቸውን አመራሮችና አባላት እንዲሁም በሰልፉ የተሳተፉትን የህብረተሰብ ክፍሎች አመስግነዋል፡፡ መንግስት በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ፓርቲያቸው ያነሳቸው ጥያቄዎች ካልተመለሱ በተጠናከረ መልኩ ተቃውሚችንን እናሰማለን ብለዋል፡፡

የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮችና የስራ አስፈፃሚ አባላት በሰልፉ ላይ ተሳትፈዋል፡፡ የተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት በሰልፉ ከመሳተፍ ባለፈ በሰላም እንዲጠናቀቅ የማስተባበር ስራ ሲያከናውኑ ውለዋል፡፡ በተለይም የሁሉም የአንድነት ፓርቲ የአዲስ አበባ ዞን የወረዳ አመራሮች ንቁ ተሳትፎ ነበራቸው ፡፡








# ወላይታ ዞን አረካ ከተማ ሙስናና ህገወጥ እስር እንዳለ ተጠቆመ

በአቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ የትውልድ ቦታ በሆነው በወላይታ ዞን አረካ ከተማ ለስኳር ፋብሪካ የሚውል እንጨት የጫኑ መኪናዎችና ጋሪዎች በህገወጥ መንገድ መታሰራቸውን የከተማዋ ነዋሪዎች ለፍኖተ ነፃነት አስታውቀዋል፡፡
እንደነዋሪዎቹ ጥቆማ በከተማው ካሉ አነስተኛ የእንጨት ሥራ ኢንዱስትሪዎች ጂንካ ከተማ ለሚቋቋመው ስኳር ፋብሪካ ግንባታ የሚውል ሞራሌ ገዝተው የሚሄዱ ሁለት ኦባማ አይሱዙ መኪናዎች ከነሹፌራቸው እንዲሁም አምስት ጋሪዎች ከነነጂዎቻቸው ዓርብ ግንቦት 23 ቀን 2005 ዓ.ም በአረካ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ ሾፌሮቹ "እኛን ለምን ታስሩናላችሁ ህጋዊ ደረሰኝ ይዘናል፤ የጫነው እንጨት ጂንካ ለሚገኘው ስኳር ፋብሪካ ግንባታ የሚውል ሞራሌ ነው" ቢሉም ሰሚ አላገኙም የሚሉት የከተማዋ ነዋሪዎች እስሩ የተፈፀመው ሙስና በፈለጉ የመንግስት ሃላፊዎች እንደሆነ እንደሚጠረጥሩ አስረድተዋል፡፡
ሾፌሮቹ በታሰሩበት ወቅት እንግልት እንደተፈፀመባቸውና ተንቀሳቃሽ ስልኮቻቸውን በፖሊሶች እንደተቀሙም ነዋሪዎቹ አጋልጠዋል፡፡ ከዚህቀደም ጂንካ በመገንባት ላይ ላለው ፋብሪካ ግብአት የሚሆነውን እንጨት ሲያጓጉዙ እንደነበር ሆኖም በጥቅም የተሳሰረ ሌላ አቅራቢ እድሉን እንዲጠቀም በሚል እስሩ እንደተፈፀመ የከተማዋ ነዋሪዎች ጥርጣሬያ ቸውን ተናግረዋል፡፡ ጨምረውም በኮንትሮባንድ የሚያዙ መኪናዎች በፐርሰንት እንደሚቀጡና የደን ውጤቶች ህገወጥ ናቸው ተብለው ሲያዙ ገቢዎች በሃ ራጅ ተሸጦ ገንዘቡን ኃላፊዎቹ እንደሚከፋፈሉት እንደሚያውቁም ለፍኖተ ነፃነት አስታውቀዋል፡፡
የከተማው አስተዳደር አቶ ቢረጋ ብርሃኑን በስልክ አግኝተን ስለጉዳዩ የሚያውቁት ነገር እንዳለ ጠይቀናቸው "እኛ ከህግ ውጪ ምንም አላደረግንም የደን ውጤቶች ንግድ ደንን ስለሚያራቁት ተከልክሏል፡፡ አረካ ከተማ እነዚህን ምርቶች ፈቃድ አውጥተው የሚነግዱ ሱቆችም የሉም" ብለዋል፡፡
እነዚህ ምርቶች የመንግስት የልማት ድርጅት ለሚያሰራው የስኳር ፋብሪካ የሚውሉ ምርቶች አይደሉም ወይ ተብለው ሲጠየቁም "እኛም የመንግስትንና የህዝቡን ሃብት መጠበቅ አለብን የፋብሪካው ከሆነ ፋብሪካው ደብዳቤ ይፃፍልን" ብለዋል፡፡ በፍኖተ ነፃነት በተደረገው ማጣራት በአረካ ከተማ ህጋዊ ፍቃድ አውጥተው እንጨትና የእንጨት ውጤቶችን የሚነግዱ ሱቆች እንዳሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
ተፈፀመ ስለተባለው እስርና ከሙስና ጋር ስላለው ትስስር ለማረጋገጥ ወደ ከተማዋ ፖሊስ አዛዥ ብንደውልም ስልካቸው አገልግሎት ባለመስጠቱ ምላሻቸውን ለማካተት አልቻልንም፡፡

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# ‹‹እናትና አባቴ የሁለት ልጆቻቸው ሀዘን ሰብሯቸው በቅርቡ በሞት ተለይተውናል››

## ወጣት እዮብ ከበደ የሰኔ አንድ ተማፅታት ማህበር ሰብሳቢ



ፍኖተ ነፃነት፡- ሙሉ ስምህን በመግለጽ ራስህን ከአንባቢዎቻችን ጋር አስተዋውቅ

ወጣት እዮብ፡- ሙሉ ስሜ እዮብ ከበደ ይባላል፣ባለ ትዳርና የልጆች አባት ስሆን በደርግና በኢህአዴግ አገዛዝ ሁለት ወንድሞቼን በግፍ ተነጥቂያለሁ። የ1997 ምርጫን ተከትሎ መንግስት በግፍ ለገደላቸው ሰማዕታት መታሰቢያ እንዲሆን የተቋቋመውን ማህበር በሰብሳቢነት እያገለገልኩ እገኛለሁ።

ፍኖተ ነፃነት፡- በሰኔ ወር በሞት የተነጠቅከው የቤተሰብህ አባል ማን ነው?

ወጣት እዮብ፡- በሞት የተነጠቅኩት ታላቅ ወንድሜን ሚልዮን ከበደን ነው።

ፍኖተ ነፃነት፡- እንዴት ነበር ህይወቱን ያጣው?

ወጣት እዮብ፡- ሁላችንም በወቅቱ እንዳደረግነው ወንድሜም ድምጹን ለቅንጅት ሰጥቷል። ህዝቡ በመጨረሻ ድምጼን ተነጥቂያለሁ በማለት ለተቃውሞ ወደ አደባባይ ሲወጣ ወንድሜም ህዝቡን ተቀላቅሏል። ተቃውሞውን ለማሰማት አደባባይ የወጣውን ወንድሜን መንግስት መሳሪያ በመተኮስ ለህልፈተ ህይወት ዳርጎታል።

ፍኖተ ነፃነት፡- የወንድምህን የፖለቲካ ተሳትፎ እንዴት ትመዝነዋለህ?

ወጣት እዮብ፡- ወንድሜ የፖለቲካ ተሳትፎ የለውም ነገር ግን እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወጣት እንደውም ሳር ቅጠሉ ማለት ይቻላል ድምጹን ለቅንጅት ሰጥቷል። ከዚህ ውጪ የተለየ የፖለቲካ ተሳትፎ አልነበረውም።

ፍኖተ ነፃነት፡- እንደምታስታውሰው በወቅቱ ስልጣን ላይ የነበሩትን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ጨምሮ የበታች ሹማምንቶች የተገደሉት ሰዎች ባንክ ለመዝረፍ፣ከፖሊስ ላይ መሳሪያ ለመንጠቅና ንብረት ለማውደም በመሞከራቸው የተገደሉ ናቸው ማለታቸው አይዘነጋም።እንደው ወንድምህ እንዲህ አይነት እንቅሰስቃሴ ውስጥ ነበር?

ወጣት እዮብ፡- ባንክ ሲዘርፉ እንዳልከውም መሳሪያ ለመንጠቅ ሲሞክሩ መገደላቸው ተነግሯል። ነገር ግን የባንክ ሃላፊዎች ፣ጥበቃዎችና ሌሎችም በሰጡት ምስክርነት ሟቾቹ ተቃውሟቸውን ከማሰማት ውጪ የተባሉትን ነገሮች አለመፈጸማቸውን አስረድተዋል። የሚበዙት ወጣቶች በተገደሉባቸው ቦታዎችም ባንኮች የሉም። ግድያው በብዛት የተከሰተው በአውቶብስ ተራ፣ፋሲል ፋርማሲ አቅራቢያ፣በመሳለሚያ ፣በሰባተኛና አብነት አካባቢ ነበር።በእነዚህ ቦታዎች ደግሞ ባንኮች የሉም።

ፍኖተ ነፃነት፡- ወንድምህ የተገደለ ዕለት አንተ የት ነበርክ?

ወጣት እዮብ፡- ወንድሜ የተገደለ እለት እኔ ሰፈር አካባቢ ነበርኩ ።በሚገርም ሁኔታ የወንድሜን መሞት ሳላውቅ በጥይት የተገደሉ ሌሎች ሰዎችን አስከሬን ሳነሳ ነበር። በተለይ በጣም የማስታውሰው ከጉራጌ ክልል የመጣ አንድ ሙሽራ ከሰርጉ ተመልሶ ቤቱ ሊገባ ሲል መንገድ ላይ ተመትቶ ህይወቱ አልፏል። እኔ እሱን እያነሳሁ ነበር። አንድ ሰው ወደ እኔ መጥቶ ሚልዮን እጁ ላይ ተመትቶ በአምቡላንስ ሆስፒታል ተወስዷል አለኝ። እናቴን አስከትዬ ወደ ጥቁር አንበሳ አመራሁ ሆስፒታሉ ውስጥ እንደደረስን በአጋጣሚ በካርድ ክፍሉ የወንድሜ ስም ተጽፎ አየሁ።ይህ ካርድ የወንድሜ ነው ምንድን ነው የሆነው ብዬ ስጠይቃቸው ወደ ውስጥ እንድገባ አድርገውኝ የሆነውን ሁሉ ነገሩኝ። ሀዘኔን በውስጤ ይዤ እናቴን ወደ ቤት እንሂድ እዚህ የለም አልኳት። የጎረቤት ሰው ምን እንደተፈጠረ በመስማቱ ቀድሞን ተዘጋጅቶ ይጠብቀን ነበር፡ ፡በቃ መጨረሻ ላይ ለእናታችን የሆነውን አረዷት።

ፍኖተ ነፃነት፡- ወንድምህ ምንድን ይሰራ ነበር፣ባለትዳር ነበር?

ወጣት እዮብ፡- የአንበሳ አውቶብስ ሰራተኛ ነበር። ለቤተሰቡ የሚረዳ በጣም ትሁት እናትና አባቱን የሚያከብር ነበር። ትዳር ግን ገና አልመሰረተም ነበር።

ፍኖተ ነፃነት፡- ሰኔ አንድ በመጣ ቁጥር ወደ አእምሮህ የሚመጣው አሳብ ምንድን ነው;

ወጣት እዮብ፡- ሰኔ አንድ ብቻ አይደለም። በደርግ ዘመን አምቦ እርሻ ኮሌጅ የሚማር ወንድም ነበረኝ፣እርሱን ደርጎች በጥይት ደብድበው ገድለውታል። ኢህአዴግም በተመሳሳይ መልኩ ሌላኛውን ወንድሜን ገድሎታል ይህንን ሁኔታ እኔ ታሪክ ተደገመ በማለት ነው የምገልጸው። እናትና አባቴ የሁለት ልጆቻቸው ሀዘን ሰብሯቸው በቅርቡ በሞት ተለይተውናል። እናቴ በሄደችበት ደረቷን ስትመታ አባቴም በሀዘን ተቆራምዶ ህይወቱ አልፏል።

ፍኖተ ነፃነት፡- ኢህአዴግ አዲስ አበባን በተቆጣጠረ ማግስት በኢህአፓነት የተገደሉ ወጣቶችን አስከሬን እያስወጣ ወላጆቻቸውን ማስለቀሱ አይዘነጋም ነገር ግን የቀድሞውን አሳዛኝ ክስተት መድገሙ ምን ስሜት ፈጠረብህ?

ወጣት እዮብ፡- እኔ እኮ ለሁለቱም መንግስታት ማንነት ማስረጃ ነኝ። እናቴ ለመጀመሪያ ልጇ ለቅሶ እንድትወጣ ሲነገራት እምቢ ብላቸው ነበር። እናቴ ይህ ነገር ሊደገም እንደሚችል የጠረጠረች ይመስለኛል፡ ፡ ፎቶግራፍ ይዛ እያለቀሰች በቴሌቭዥን መታየት አልፈለገችም። ትልቁ ነገር ሰውን ለፖለቲካ ፍጆታ ማዋል ሳይሆን በአደባባይ ያወገዙትን ሆኖ አለመገኘት ነው። የሁለቱም መንግስታት ድርጊት የሚያሳየን አምባገነኖች መሆናቸውን ነው።

ፍኖተ ነፃነት፡- ኢትዮጵያ ሰላም፣ፍትህ የሰፈነባትና ዜጎቿ በፖለቲካ አመለካከታቸው የጥይት ሰለባ የማይሆኑባት ሆና አያታለሁ የሚል እምነት አለህ?

ወጣት እዮብ፡- በእግዚአብሄር የማምን በመሆኔ ተስፋ አደርጋለሁ። ባሏት ቆራጥ ልጆቿ ትግል እንዲህ አይነት አገር ይኖረናል ብዬ አምናለሁ፤ ይህንን ለማየት ግን ጠንከር ያለ ሰላማዊ ትግል ማድረግ ያስፈልጋል። ያንግዜም ዜጎች የመሰላቸውን ሃሳብ በነጻነት ያሰራጫሉ፣ወጣቶች ያለ መሳቀቅ ይኖራሉ፣ እናቶች ስለ ልጆቻቸው ስጋት አይገባቸውም ፣በኮንቴነር እየተጫኑ ለስደት የማይዳረጉ በመሆናቸው አሰቃቂ ዜና የምናደምጥበት ወቅት ያከትማል።

ፍኖተ ነፃነት፡- በሰብሳቢነት ስለ ምትመራው ማህበር እንነጋገር በአሁኑ ሰዓት የምትገኙበት ሁኔታ ምን ይመስላል?

ወጣት እዮብ፡- ማህበሩ ላይ የተለያዩ ጫናዎች እየተደረጉበት የሚገኝ ቢሆንም እስካሁን ድረስ እየሰራን እንገኛለን። በቅርቡ አንድ ሰው ደውሎ በአንድ ፖሊስ ጣብያ ውስጥ ቀጥሮኝኝ ‹‹የሰማዕታት ማህበር እያልክ የምታደርገውን እንቅስቃሴ ብታቆም ይሻልሃል››አለኝ፡ ፡ ማስፈራሪያውን ከቁብም ሳልቆጥር በፈለግኑት መንገድ የመደራጀት መብት እንዳለኝ በመጥቀስ የፈለጉትን አይነት ውሳኔ ማሳለፍ እንደሚችሉ በመንገር ከአላማዬ እንደማያስተጓጉሉኝ ነግሪያቸዋለሁ።

ፍኖተ ነፃነት፡- ማህበሩን ለመመስረት የበቃችሁበት ምክንያት ምንድን ነበር?

ወጣት እዮብ፡- ማህበሩን የመሰረትነው ተመሳሳይ በደል የተፈጸመብን ሰዎችና ቤተሰቦች ነን። የእነዚህ ልጆች ደም ነገ ሳይደገም ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር እንዲኖርና በእነሱ ይብቃ ለማለት ማህበሩን መስርተናል።

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
# UNITY FOR DEMOCRACY AND JUSTICE PARTY (UDJ)

# አባሎቻችንና አመራሮቻችን ላይ እየተወሰደ ያለውን ህገ-ወጥ እስርና ድብደባ በህዝባዊ ንቅናቄ እንታገለዋለን፣ እናስቆመዋለን!!!

## አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ(አንድነት) የተሰጠ መግለጫ



ፓርቲያችን አንድነት ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የሚገባቸውን ዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደር፣ ፍትህ፣ ነፃነትና እኩልነት እንዲጎናፀፉ በማለም በፅናት ትግሉን ቀጥሏል፡፡ በዚህ ሂደትም ቁርጠኛ አመራሩና አባላቱ መስዋእትነት ከፍለዋል፡፡ አሁንም እየከፈሉ ይገኛሉ፡፡

በተለይም የፓርቲያችንን መዋቅር ለማፍረስ እረፍት የሌለው ገዥ ፓርቲ በክልሎች የሚገኙ አመራሮቻችንን ማሰር፣ መደብደብ፣ ማግለልና ስም እየለጠፉ ማስፈራራት ዋና ተግባሩ አድርጎ እየሰራበት ነው፡፡ አባሎቻችንና አመራሮቻችንም ሳይበገሩ በቁርጠኝነት ትግሉን በሰላማዊ መንገድ በመግፋት ላይ ይገኛሉ፡፡

ሰላማዊ ትግል የሚያስከፍለው ዋጋ ሁሉ ለመክፈል ቁርጠኝነቱም አላቸው፡፡
በየጊዜው በአባሎቻችንና አመራሮቻችን ላይ እየተወሰደ ያለው ህገ-ወጥ የሰብዓዊ መብት ገፈፋ፣ ጭካኔ የተሞላበት ግርፊያና ድብደባ እንኳን መንግስት ነኝ ከሚል አካል ቀርቶ ከጨካኝ ወንበዴ የሚጠበቅ አይደለም፡፡

ይህንን ድርጊት ከመቃወም በዘለለ የህዝባዊ ንቅናቄ በመፍጠር ማስቆም እንደሚገባ አጠንክረን እናምናለን፡፡
ህዝብ ላይ የሚፈፀም ግፍና በደል ሊፈታና ሊወገድ የሚችለው ግፍና በደል ባንገፈገፈው ህዝብ ተከታታይና ትርጉም ያለው ትግል ነው፡፡

በፓርቲያችን አመራሮች ከሚፈፀሙ ህገ-ወጥ የገዥው ፓርቲ ግፎች አንዱ አቶ ተገኝ ሲሳይ በተባለ የምእራብ አርማጭሆ የአንድነት ሰብሳቢ ላይ የተፈፀመው ህገ-ወጥ እስርና በታሰረበት የተፈፀመበት ከፍተኛ ድብደባ ነው፡፡ አቶ ተገኝ ሲሳይ ክስ ሳይመሰረትበት የአደራ እስረኛ ነው በሚል ከመጋቢት 17 ቀን 2005ዓ.ም ጀምሮ አፍነው በመውሰድ፤ እጁ እስከሚሰበር በመደብደብና ህክምና እንዳያገኝ በማድረጋቸው በህይወት መቆየቱ አጠያያቂ እስከሚሆንበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

በአዲስ አበባም የወረዳ 19 ምክትል ሰብሳቢ የሆነው ወጣት ባህሩ ራህመቶ ከቤቱ ታፍኖ ተወስዶ የት እንደገባ ሳይታወቅ ከቆየ በኂላ ማዕከላዊ ይገኛል፡፡ ፓርቲያችን አመራሮችና አባላት ላይ እየተፈፀመ ያለውን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት፣ ህገ-ወጥ እስርና ድብደባ ከማውገዝም ባሻገር ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በመሆን ትግሉን እንቀጥላለን፡፡
በህዝባዊ ንቅናቄ አፈናና እስሩን እንታገላለን፡፡ ይህንንም በቅርቡ ይፋ የምናደርግ ይሆናል፡

*ምንም ዓይነት ርምጃ ከትግል መስመራችን ፈቀቅ አያደርገንም!!!*
አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
ግንቦት 25 ቀን 2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67



አንድነት ፓርቲ ማተሚያ ማሽን በመግዛት
የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣን ህትመት ለማስቀጠል
የገቢ ማሰባሰቢያ መርሀግብር ጀምሯል
እርስዎም ፦
. ኩፖን በመግዛት
. የቃልኪዳን ሰነድ በመሙላት
. አቢሲኒያ ባንክ ጠመንጃ ያዥ ቅርንጫፍ የባንክ ሒሳብ ቁጥር 47 ገቢ በማድረግ አጋርነትዎን ያረጋግጡ
ለተጨማሪ መረጃ
0933-89-17-66 እና
0933-89-17-67 ይደውሉ
udjparty@gmail.com
ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ወደ ህትመት እንድትመለስ በመርዳት መረጃ የማግኘት መብትዎን ያስከብሩ!!
ፍኖተ
ነፃነት
የኢትዮጵያን ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!
አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ